ኩዌር ኢትዮጵያ
QUEER ETHIOPIA



ፍቅር መስዋእት ነፃነት

# ማንነት እና ስደት

## የኩዌር ኢትዮጵያውያን ስደተኞች የፅናት እና የጀግንነት ታሪኮች

ልዩ እትም- ዓለምአቀፍ የስደተኞች ቀን

ሰኔ 13 2018

# መግቢያ
# የነፃነት ፍልሚያ

ይህ ልዩ አትም ሰብአዊ ክብርን ፍለጋ ተቋማዊና ማኅበረሰባዊ ጥላቻን እንዲሁም ሥነ-ልቦናዊ ቀውስን ሸሽት የተሰደዱ ኩዊር ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ልብ የሚነካ የግል ምስክርነት ነዉ። ይህ አትም ከጃምዚ፣ ከሄለን እና ከግሬስ ጋር በተደረጉ ጥልቅ ቃለ-መጠይቆች አማካኝነት በሃይማኖት፣ ራስን በመቀበል፣ ከመኖሪያ በመፈናቀል እና በስደት ዓለም "ቤት" ማግኘት መካከል ያሉትን ውስብስብ ትስስሮች ይዳስሳል።

በአፍሪካ ለሚገኙ በርካታ ኩዊር ግለሰቦች፣ ማንነት ማለት በእውነተኛ ማንነት እና ተቋማዊ ወይም ማኅበረሰባዊው በሆነዉ ልማዳዊ መረዳት መካከል ያለዉን አስጨናቂ ጫና የመጋፈጥ ጦርነት ነው። ይህ አትም ከኢትዮጵያ የክፍለ-ሀገር ከተሞች እና ከዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ወደ ኬንያ ለመሰደድ የተገደዱ ኩዊሮችን ታሪክ የያዘ ሲሆን፤ ታሪኮቹ ቃል በቃል የተቀመጡ እና ያልተቀነባበሩ ናቸው። የህይወት ልምዳቸዉ ፍቅር፣ ፅናት እና እምነት ፍጹም በሆነ መገለል ውስጥ እንኳን ሊጠፉ እንደማይችሉ ያስታውሱናል።

በዚህ አትም ውስጥ የተካተቱት ሁሉም ምስሎች፣ ባለታሪኮቹ  የዕለት ተዕለት ሕይወታቸውን ለማሳየት ሲሉ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ በራሳቸዉ ያነሷቸዉ ስራዎች ናቸው።



ክፍል 1

## ራስን ፍለጋ


### የጃምዚ ታሪክ






“

**የኔ ግን ከእግር ጥፍሬ እስከራስ ጸጉሬ የሚነዝረኝ ነው እና ከልጅነት የጀመረ ተፈጥሮዬ ነው።**



**ራሴን መቀበሌ ትልቁ ስኬቴ እንደሆነ ስለማምን ከምንም በላይ ያኮራኛል።**

የእኔ የምላትን ሰው በመንገድ ላይ ይዤ ስሄድ፥ ስለተመሳሳይ ጾታ ጮክ ብዬ ሳወራ፥ እኔን የሚገልጹኝን ሙዚቃዎች በስፒከር ስከፍት፥ የሚሰድበኝም የሚያሯሯጠኝም ወይ እንደልዩ ፍጡር የሚያየኝ እንደሌለ ሳይ የበለጠ ማንነቴን በነጻነት የምሆንበት ቦታ እንዳገኘሁ አወቅኩ።

## ራሴን የማወቅ ጉዞዬ

ሴቶች እንደሚማርኩኝ ያወቅኩት የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ ነው። በእርግጥ ሴት የምታምር እና የምትደነቅ ፍጡር በመሆኗ ሁላችንም ብንማረክ አይደንቅም። ብዙ ጊዜዬን ከወንዶች ጋር ስለማሳልፍ የእነሱ ተጽእኖ ይመስለኝ ነበር። እየቆየሁ ግን ከተወሰኑ የሴት ጓደኞቼ ጋር ስናወራ እነሱ ሴትን የሚያደንቁበት መንገድ እና የእኔ የተለያየ እንደሆነ ተረዳሁ። “እኔ ብቻ ነኝ ወይስ እናንተም የኔ አይነት ስሜት ይሰማችኋል?” ስላቸው እነሱ ቀለል አድርገው ነበር የሚያልፉት፥ የኔ ግን ከእግር ጥፍሬ እስከራስ ጸጉሬ የሚነዝረኝ ነው እና ከልጅነት የጀመረ ተፈጥሮዬ ነው።

ያደግኩት አስራ አንድ አባላት ባሉት ትልቅ ቤተሰብ ነው። ደስ የሚል ቤተሰብ እና አድገት ነበረኝ። ወንዳወንድነቴ ራሴንም ከመቀበሌ በፊት የነበረ ነው፤ ሰዎችም የሚያውቁኝ በዛ ነው። ምናልባት ክልል ውስጥ ስላደግኩ ሊሆን ይችላል፤ ሰዎች ስለተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነት ብዙም እውቀት ስላልነበራቸው ወንዳወንድነቴ ጥያቄ ፈጥሮ አያውቅም። ከወንዶች ጋር ኳስ እየተጫወትኩ በማደጌም የእሱ ተጽእኖ እንጂ እውነትም ሴት ትወዳለች ብሎ የሚጠረጥር አልነበረም። ጸጉሬን አሳጥሬ እንደወንድ እየለበስኩም ስፖርተኛ ነች ተብዬ አታለፋለሁ እንጂ በጾታዊ ዝንባሌዬ ላይ ጥርጣሬ አልገጠመኝም።

አሁን አሁን ታናሽ እህቴ ሌዝቢያን መሆኔን እንደምታውቅ እጠረጥራለሁ። የተቀሩት የቤተሰብ አባሎች እንኳን ወንዳወንድ እንደሆንኩ ነው የሚያውቁት፥ አባቴ ጸጉሬ ሲያድግ ምነው ተቆረጨው የሚል አይነት አባት ነው። ወንድሞቼ ለራሳቸው ልብስ ገዝተው ሲመጡ የነሱ አይነት ገዝተውልኝ ይመጣሉ። ያ ማለት ግን ቢያውቁ ይቀበሉኛል ማለት አይደለም፥ እነሱ እንኳን ቢቀበሉ በማህበረሰብ ግፊት የሚረበሹ ይመስለኛል።

## ጉዞ ወደአዲስአበባ

የእኔ አይነት ትግል ውስጥ ያሉ ሰዎች እንዳሉ ያወቅኩት አዲስአበባ ከመጣሁ በኋላ ነው። ሶሻል ሚዲያ መጠቀም ስጀምር እና ሰዎችን ስተዋወቅ ደግሞ የብቻዬ ርግማን እንዳልሆነ ተረዳሁ። የማማከረው ሰው ማግኘቴ እንድረጋጋ ስላደረገኝ ደስ አለኝ። ከዛ በፊት ስለዚህ ጉዳይ የማዋራው ሰው አልነበረኝም። እነዚህ በሶሻል ሚዲያ የተዋወቅኳቸው ሰዎች ግን “የግብረሶዶምን እንቃወማለን!” ዘመቻ ሰአት እንኳን ከሀገር እስከወጣ ድረስ አብረውኝ ነበሩ። ያ ወቅት ለማህበረሰባችን በተለዩ ደግሞ ወንዳወንድ መገለጫ ላለን ሴቶች ከባድ ነበር። ይሁንና ክልል እያለሁ ከነበርኩበት ብቸኝነት አንጻር የአዲስ አበባ ሰው ለማውራትም ሆነ ጓደኛ ለማግኘት የተሻለ ነበረ። በዛው ልክ ሰው በተገደበ መልኩ ስለእኛ ማንነት ጭፍን አረዳድ እና ጥላቻ ያላቸው ብዙ ሰዎች ስላሉ ኢላማ ለመደረግ ቀላል ነበር።

በ2015 በተነሳው የ“ግብረሰዶምን እንቃወማለን” ዘመቻ ሀምሌና ነሀሴን ተሸብረን ነበር የቆየነው። በተለዩ እኔ አለባበሴና ሁኔታዬ ያው እንደገለጽኩት ወንዳወንድ በመሆኑ ስራ መስራትም አልቻልኩም። መንገድ ላይ እያስቆሙኝ “ሌዝቢያን ነሽ?’ እያሉ የሚጠይቁኝ ሰዎች ነበሩ። ከሴት ጓደኞቼ ጋር ካፌ ውስጥ መቀመጥ አስከቸገር ደርሼ ነበር። “እሷ እንዲህ ነች እንደዚህ ታደርግሻለች፥ እንዳታበላሽሽ ከዚች ራቂ” የሚሉ ነበሩ። አስቀያሚ ስድቦች የሚሰደቡ እና ለመደባደብ የሚሞክሩ ራሱ አሉ። አካላዊ ጉዳት ባይደርስብኝም አእምሯዊ እና ስነልቦናዊ ጥቃት ግን ደርሶብኛል።



“ በጨለማ ዉስጥ ብርሀንን አገኘሁ።




“ እግር ኳስ ከአለም መደበቂያዬ እንጂ ሙሉ ታሪኬ አልነበረም። ከጥላቻቸዉ ጠብቆኛል፤ በፍርዳቸው የተሰበርኩትን ጠግኖኛል። ዛሬ ሙሉ እኔነቴን ሆኜ ከሜዳው እወጣለሁ።

አንዴ የጓደኛዬን ልደት ልናከብር ከስራ በኋላ ተገናኘን፥ መዝናኛ ቤት ሆነን እየተጫወትን፥ ከአጠገባችን አምስት ስድስት የሚሆኑ ገዘፍ ያለ ሰውነት ያላቸው ወንዶች ተቀምጠዋል፥ ትንሽ ቆይቶ አስተናጋጇ እኔ መጸዳጃ ቤት ስሄድ ጠብቃ ለጓደኛዬ ወንዶቹ ሲያበድቡኝ እያቀዱ እንደሆነ ሲያወሩ እንደሰማች እና እንድንጠነቀቅ ነገረቻት። ፀጉሬ ሁሉ በአለባበሴ የተነሳ ነው እንጂ ሌላ ያደረግኩት ነገር ኖሮ ወይንም እኔ በትክክል ሴዝቢያን እንደሆንኩ አውቀው አልነበረም። ጓደኛዬም ሴዝቢያን ብትሆንም ከጓደኝነት ያለፈ ግንኙነት አልነበረንም፥ እንደአጋጣሚ ከአጠገባችን ሌሎችም ወንዶች ስለነበሩ ህይወቴ ተረፈ እንጂ እስከወጣ ጠብቀው ሊጎዱኝ ፈልገው ነበር። ጭራሽ አንዱ አጠገባችን መጥቶ ያለፍቃድ ተቀመጠና ጓደኛዬን እኔ ሴዝቢያን እንደሆንኩ እና ከእኔ እንድትርቅ ካልሆነ እንደማበላሻት ፀመክራት ጀመር። ጓደኛዬም ሴዝቢያን ብትሆንም አለባበሷ በተለምዶ የሴት የሚባለው በመሆኑ ብቻ እሷን ሳይጠረጥር እኔን ግን ሰው ፊት ፀናገረኝ ጀመር። ጓደኛዬም ስለማያውቀው ነገር እንዳፀዘባርቅ አስጠንቅቃ ዞር እንዲል ልታደርገው ብትሞክርም ጭራሽ እልህ እየያዘውና እየባሰበት መጣ፥ የዛን ግዜ እኔ በጣም እየተሸበርኩ ስለነበር እሱን ለማረጋጋት እና በሰላም ለመውጣት ብዬ በእርጋታ ምን ሳደርግ አይቶኝ እንደወነጀለኝ ጠየቅኩት። የዛኔ ሌላ ጠረጴዛ ላይ የነበሩ ሌሎች ወንዶችም ወደእኛ መጡና በተሰሳተ መረጃ ሰውን መወንጀል ልክ እንዳልሆነ በመንገር “ሲሰሳሙ ወይ ያልተገባ ነገር ሲያደርጉ አይተኻቸዋል?’ ብለው አፋጠጡት። “እኛ የተለየ ነገር አላየንም አንተ ምን አድርጉ ነው የምትላቸው?” ብለው ሲሉት በንዴት ወደቦታው ተመለሰ፥ ቢሆንም ግን እነሱ ሳይወጡ አንወጣም ብለን ሳንፈልግ እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ድረስ ቆየን፥ ከወጡም በኃላ አስተናጋጇ እንደሄዱ ስታረጋግጥልን ነው የግል ታክሲ ጠርተን ወደየቤታችን የሄድነው።

ሌላ ጊዜ ደግሞ ቁምጣና ኮፍያ ያለው ሹራብ እንደማንኛውም ሰው ለብሼ ከባንክ ቤት ወጥቼ ቤት ልደርስ ስል መንገድ ላይ እንደዚሁ ወንዶች አስቁመውኝ “ለምንድን ነው እንደዚህ የምትለብሺው?” ብለው ጠየቁኝ፥ እኔም ስፖርተኛ ስለሆንኩ ሌላ ልብስ መልበስ ስለማይመቸኝ እንደሆነ ነገርኳቸው። ያን ሰሞን ደግሞ “ግብረሰዶምን እንቃወማለን” አመጽ ተነስቶ ስለነበር ሁሉም ሰው አካባቢውን በአይነቁራኛ ነበር የሚመለከተው፥ ስለዚህ የሚሉኝን ነገር ከመከራከርና ራሴን ከመከላከል ይልቅ “እሺ ልክ ነህ” እያልኩ ለመስማት ዝግጁ ነበርኩ። በየፍሬንድ እንዳለኝ ሲጠየቀኝ በራስ መተማመን “ልደውልለት ታናግረዋለህ?” ብዬ የአውር ድንብሬን መልሼ ጠየቄዋለሁ። የዛን ሰአት ተረጋጋና “በቃ እንዲህ አትልበሺ፥ እንደሴት ሁኚ” ብሎ “መክሮኝ” ለቀቀኝ። ያን እለት እንዴት ቤት እንደገባሁ አላውቅም፥ ነፍሴ በፍርሀት ከሰውነቴ ልትወጣ ነበር፥ ከዛ በኋላ መንገድ ላይ ስሄድ እንደሌባ ግራና ቀኜን እያየሁ ሆነ የምሄደው። ነጻነት አጣሁ፥ ሰው ሳይጠራኝ የጠራኝ እየመሰለኝ፥ የሰው እግር ዱካ ከኋላዬ እየተሰማኝ አእምሮዬ ተረበሸ። ከዛ በኋላ ነበር የአሁን ፍቅረኛዬ ጋር በዋትሳፕ እናወራ ስለነበር የገጠመኝን ስነግራት እንደምንም ብለሽ ኬንያ ከመጣሽ እዚህ ያለውን ነገር በኔ ጣይው ብላኝ በዚች ቃል ብቻ ተነስቼ በጥላቻው ሰሞን ሀገር የለቀቅኩት።

> "ነጻነት አጣሁ፥ ሰው ሳይጠራኝ የጠራኝ እየመሰለኝ፥ የሰው እግር ዱካ ከኋላዬ እየተሰማኝ አእምሮዬ ተረበሸ።"
>
> -ጃምዚ

በነዚህ ችግሮች ሀገሬን ትቼ እዚህ ኬንያ ስመጣ ነጻነቴን አገኘሁ፥ የእኔ የምሳትን ሰው በመንገድ ላይ ይዤ ስሄድ፥ ስለተመሳሳይ ጾታ ጨካ ብዬ ሳወራ፥ እኔን የሚገልጹኝን ሙዚቃዎች በስፒከር ስከፍት፥ የሚሰድበኝም የሚያሯሯጠኝም ወይ እንደልዩ ፍጡር የሚያየኝ እንደሌለ ሳይ የበለጠ ማንነቴን በነጻነት የምሆንበት ቦታ እንዳገኘሁ አወቅኩ። አሁን በጣም ነጻ ነኝ። ከመጣሁ አሁን አራት አመት ሊሆነኝ ነው።


## ራስን መቀበል፥ ነጻነት እና የፍቅር አጋርን ማግኘት

ለእኔ ማንነቴ ጥንካሬዬ ነው ብዬ ነው የምገልጸው። ኢትዮጵያ እያለሁ ብቸኛ ከመሆኔ በተጨማሪ ታምሜያለሁ ወይስ ምን ሆኛለሁ ብዬ ራሴን እስከመጠየቅ ደርሼ አውቃለሁ። ምክንያቱም ባደግኩበት የክልል ከተማ እንደ አዲስአበባ የኔ አይነት ሰው አልነበረም፤ ቢኖርም አላውቅም። የማወራው ሰው ስለሌለ ብቸኝነት ይሰማኝ ነበር። ይሄ ስሜት ደግሞ ከልጅነቴ የነበረ ስለሆነ የምቆጥረው እንደችግር ነበር። “ለምን እኔ ብቻ?” የሚለው ስሜት ያስጨንቀኝ ነበር። አዲስ አበባ ስሄድ ግን የኔ አይነት ብዙ ሰዎች በመኖራቸውና ዘና ብለው ራሳቸውን ተቀብለው ሲኖሩ በማየቴ ፍቅር ስርዓተ ጾታ እንደሌለው አመንኩ። ይሁንና አዲስ አበባ ነጻነትን የማወቂያ መንገድ እንጂ ነጻ መሆኛ አልነበረችም።

በእኛ ማህበረሰብ የፍቅር አጋር ማግኘት ሌላው ራስ ምታት ነው፥ ራስን መቀበል ደግሞ የራሱ ትግል አለው። ስለራስሽ ብዙ ነገሮች አስበሽ ኖርማል አይደለሁም እንዴ? ለምን እኔ ብቻ እንዲህ አይነት ስሜት ይሰማኛል? የሚል ግጭት ውስጥ ቆይተሽ በስንት ጭንቀ አልፈሽ መሰሎችሽን ስታገኚ ደግሞ የምትፈልጊውን ሰው ማግኘቱ እና በፍቅር ታምኖ አብሮ መሆኑ ሌላ ትልቅ ትግል እና እድል የሚጠይቅ ነው። የፍቅር አጋር ስትፈልጊ ደግሞ በመጀመሪያ ማንስ ይታመናል? በሶሻል ሚዲያ እንኳን ራሳችንን ደብቀን ነው፥ በዛ ላይ አብዛኛዎቹ የሚያዋሩሽ በውሸት አካውንት የውሸት ማንነት ይዘው ነው። አብዛኛዎቹ እኛን መስለው እኛን ሲያጠቁ የተደበቁ ተኩላዎች ናቸው። በነዚህ ምክንያቶች የተነሳ ይሄ ሰው ይሆነኛል ጥሩ ነው ብሎ ማግኘት ከባድ ነበር። የፍቅር ፍለጎትሽን በፌስቡክ ጀምረሽ በፌስቡክ አትጨርሺውም፤ የሆነ እርምጃ መሄድ አለብሽ፥ ለዛም የምትወስጂው ራሱን የቻለ ሀላፊነት አለ። እንደውም አጋር ከመፈለግ ራስን ለመቀበል ከራስ ጋር ያለው ትግል ሳይሻል ይቀራል ብለሽ ነው? በርግጥ ቀላል ሆኖ አይደለም ግን እናወዳድረው ካልን ራስን መቀበል ጋር ያለው ትግል በስንት ጣእሙ ያስብላል! በኩዊር ማህበረሰቡ ውስጥ ከባድ ነው ብዬ የማስበው ትልቁ ነገር የምታፈቅሪው እና የኔ የምትዪውን ሰው ማግኘት ነው። ሌላው ችግር እንኳን የተጋነነ አይደለም፡ ቢኖር እንኳን በተቃራኒ ጾታ አፍቃሪዎች መሀል ያለው አይነት የተለመደ ችግር እንጂ ተመሳሳይ ጾታ ስለሆንን የሚፈጠር የተለየ ችግር የለም።



“ ሰማዩ ምንም ያህል ቢጠቁር፣ ዝናቡ በጣም የቀረበ ቢመስልም፣ ነፃነት የሚጀምረው ማዕበሉን መፍራት ስናቆም እንደሆነ ራሴን አስታዉሳለሁ። ወፎች ክንፋቸውን ለመዘርጋት የተስተካከለ የአየር ሁኔታን አይጠብቁም፣ እኔም አልጠብቅም።




“ የተዋወኳት በአንድ የኲዊር የዋትስአፕ ግሩፕ ውስጥ ነበር። ሁሉንም ነገር የቀየረው ይሄ መልእክት ነዉ።



“ ለሁሉም ነገር መልስ ላይኖረኝ ይችላል፣ ነገር ግን ከእነዚህ ዛፎች ስር... እራሴን እንደገና አገኘዋለሁ። ከተፈጥሮ ጋር የማወራው ሰዎች ለመረዳት ፍቃደኛ ያልሆኑትን ነገር ስለምትረዳኝ ነው።

## የስደት ህይወት

ከኢትዮጵያ ከወጣሁ በኋላ ህይወቴ ላይ መጥፎም ጥሩም ለውጥ አለ። ከነጻነት አንጻር ካየነው፥ ኢትዮጵያ ቤቴ ውስጥ እንኳን ሆኜ ስለዚህ ጉዳዩ ለማውራት ሙዚቃ ከፍ አድርጌ ከፍቼ ነበር፥ እዚህ ግን በነጻነት ማውራትም ራሴን መሆንም እችላለሁ። ማንም ሰው የግል ጉዳዩ ውስጥ እስካልገባሽ እንዲህ ናት ብሎ ሲያገልሽ አይደለም ስራዬ ብሎም አይከታተልሽም። እዚህ ብቸኛ ችግሬ የገንዘብ ነው፥ መታወቂያም፥ የስራ ፈቃድም ስለሌለኝ ዜጋም ስላልሆንኩ፥ ጥሩ ስራና ገቢ ማግኘት አስቸጋሪ ነው። ከወር ወር የምንደርሰው ከዚህም ከዚያም እያልን ነው። ሀገሬ ደግሞ ስራ ሰርቼ ቢያንስ ራሴን ማስተዳደር እችል ነበር። ነጻነት ግን የለኝም። እዚህ ኬንያ ገና በዚህ አመት ነው ኩዊር ማህበረሰቡን ታሳቢ ያደረገ ስራ ተሰርቶ ጥቃቅን ገቢ ማግኘት የጀመርነው። በሁለት አመት ውስጥ ብዙ ስቃይ አይቻለሁ፤ ጎዳና ተዳዳሪ ነበርኩ። ሰው አላውቅም ነበር፥ የቋንቋ ችግር አለ። ስዋሂሊ ካልቻልሽ ለመግባባት ከባድ ነው፤ አብዛኛው እንግሊዝኛ ተናጋሪ አይደለም። ስራም የለም። ያው በቆይታ ብዛት እዛም እዛም እያልኩ ስራ እያፈላለኩ ሀገሩን ስላመድ የተገኘውን መስራት ጀመርኩ።

ጎዳና ላይ በነበርኩበት ሰአት ቆሻሻ መጣል እና የተለያዩ የጉልበት ስራዎችን ከወንዶች ጋር እሰራ ነበር። በማንነቴ የደረሰብኝ ነገር ባይኖርም፥ በሴትነቴ ግን የመደፈር ሙከራዎች ደርሰውብኛል፥ ያም የራሱ የሆነ ጭንቀት እና ፍርሀት ጥሎብኝ አልፏል። እየሰራሁ ለመኖር ስል አጥቂዎቼን በብልጠት የመደለል ሀላፊነት የኔ ነበር። ወንድማቸው እንደሆንኩ እየቀለድኩ ማለፍ ነበረብኝ። እግዚአብሄር ይመስገን ከዛ የከፋ ነገር ባይኖርም የጥቃት ሙከራዎች እና ስጋት ግን ነበሩ። በሰላም መተኛት ከባድ ነበር። ካልተኛሁ ደግሞ ቀን ላይ አካሌም አእምሮዬም ይደክማል። በዚህም ምክንያት ከማንነቴ ጋር ቀጥታ የተያያዘ ባይሆንም በተዘዋዋሪ ግን ስራ አለማግኘቴ እና በገንዘብ ራሴን አለመቻሌ ለጾታዊ ጥቃት ተጋላጭ አድርጎኛል። ሀገሬ ላይ በማንነቴ ባልገፋ ነጻነቴን ፍለጋ ደሀ አልሆንም ነበር፥ ሴትነቴንም ስጋት ላይ አልጥልም ነበር። ሀገሬ ላይ የመንግስት ሰራተኛ የሰው ሀይል አስተዳደር ውስጥ የምሰራ ሰው ነበርኩ። እዚህ ግን የጉልበት ሰራተኛ ነኝ። ለማንነቴ የከፈልኩት መስዋትነት ስለሆነ ባይከፋኝም፥ በሀገሬ ነጻነት አግኝቼ፥ ማህበረሰቤ ውስጥ ተቀባይነትን አግኝቼ አለመኖሬ ግን ሆድ ያስብሰኛል።

## ስለ ቤት

ለኔ ቤት ማለት ነጻነት፥ ማንነቴን ሳልደብቅ እንደፈለግኩ የምሆበንት ቦታ ማለት ነው። በዚህም ኬንያ ለእኔ ቤቴ ሆናልኛለች። ኬንያዎች ልክ እንደኢትዮጵያውያን እንግዳ ተቀባይ ናቸው፥ እና ልክ የውጭ ዜጋ እንደምንከባከበው እነሱም እንደዛው ናቸው። የማህበረሰባዊነት ስሜትን አግኝቼዋለሁ። ከየት ነው የመጣሽው ብለው አይጠይቁም፤ ከየትም ብትመጪ ይወዱሻል። በተለይ ኢትዮጲያዊ ነኝ ስትያቸው በጣም ደስ ይላቸዋል። ከማህበረሰቡ ጋር ጥሩ ግንኙነት አለኝ፤ ይወዱናል እወዳቸዋለሁ። ያከብሩኛል አከብራቸዋለሁ።

> "እንደምንም ብለሽ ኬንያ ከመጣሽ እዚህ ያለውን ነገር በኔ ጣይው ብላኝ በዚች ቃል ብቻ ተነስቼ በጥላቻው ሰሞን ሀገር የለቀቅኩት።"
>
> — ጃምዚ




“ ቆሻሻ ሳይሆን መዳን፤ ቀላል ባይሆንም ግን አስፈላጊ ነበር። ኬንያ ፈትናኛለች ግን አልተሰበርኩም። የተሸከምኩት ከፌስታል በላይ ነዉ፣ መዳኛዬም ነበር።




“ ብዙ ነገር አልነበረኝም፣ ስርአት ግን ነበረኝ። የቆጠብኳት እያንዳንዷ ሳንቲም ለወደፊት ህይወቴ የገባሁት ቃል ኪዳን ነበረች። ይህ ዝም ብሎ ሳጥን ብቻ አልነበረም፤ ተስፋዬ፣ ትግሌ እና ለተሻለ ነገ የነበረኝ ድምፅ አልባ እቅዴ እንጂ።

ሀገሬን እና ህዝቤን አሁንም እወዳለሁ፤ ሁሉንም አልወቅስም፥ ህዝቤን የማውቀው በደግነት ነው። ከክልል መጥቼ አዲስአበባ ተከራይቼ ስኖር ባዶ ሆዴን አላደርኩም። የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጠል የሆኑት ስለጉዳዩ እውቀት ከማጣት ነው እንጂ ከክፋት አይደለም። ሁሉንም አልወቅስም። አውቆ እንዳላወቀ እየሆኑ በሰው አካል አይመለከተኝም ብሎ የሰው መብት ሰይነካ የሚኖረው ሰው ብዙ ነው። ያው የተቀረው ደግሞ የኛን ሴቶች ትነካለች ብሎ ያስባል። ሴት ብወድም ሁሉንም ሴት አልወድም፤ ምርጫ አለኝ። እንዳሁ ሄጄ የሰው ሚስት፤ እህት እና እናት አልነካም። ስነስርአትም ሀይማኖትም አለኝ። የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ሆኖ ልጁን የሚደፍር ስንት አባት ነው ያለው? ተመሳሳይ ጾታ ከማፍቀር ጋር የሚመጣ የባህሪ ችግር የለም። ሰው ከመሆን ጋር የሚመጣ እና በማንኛውም የጾታ አፍቃሪ ላይ የሚከሰት መሰረታዊ ችግር ግን ይኖራል። የኛን አጋነኑት እንጂ ክፋት የሌለው ሰው የለም፤ እነሱ በሌላ መንገድ ሀጢያት ስለሚሰሩ የኛ አይነት ካልሆነ ሌላ አይነት አንቀበልም ነው። ሲጀመር ፍቅር ሀጢያት አይደለም፥ መዘሞት እንጂ። የገዛ አካሌን ለወደድኩት ሰው የመስጠት መብት አለኝ። ከዚህ በላይ ብዙ መከልከል እና አይሆንም ሊባሉ የሚገባቸው ነገሮች ኢትዮጲያ ውስጥ አሉ። ግን እንደዛም ሆኖ ሀገሬንም፥ ቤተሰቤንም፥ ህዝቤንም እወዳለሁ። ባልጠላውም የምናፍቀው ቦታ ወይም ቤቴ ግን አይደለም። ለአሁን ቤቴ ነጻነትን ያገኝሁባት ኬንያ ነች።

## የኩዊር የፍቅር ህይወት

ከፍቅረኛዬ ጋር እንደ ቅርብ ጓደኛ ማውራት የጀመርነው ኢትዮጲያ እያለሁ ነው። አብረን መኖር የጀመርነው ለእኔ ብላ ከናይሮቢ ከእናት ከአባቷ ቤት ወጥታ፥ ትንሽ ከተማ ሄዳ ስራ ተቀጥራ፤ ቤት ተከራይታ ነው። በፊት በጣም ጓደኛሞች ነበርን፤ አብረን እንሆናለን ብዬ አላሰብኩም ነበር። እግዚአብሄር አለና አብረን ሆንን። በመሀል ግጭቶች ነበሩ ግን አልፈነው እዚህ ደርሰናል። ብዙ ተፈትነናል፤ ሳንበላ ቀናቶች አሳልፈናል፤ የገንዘብ ችግር ነበር። በመሃል ስራ ለቀቀች፤ እኔም ስራ አልነበረኝም፤ በዛ የተነሳ ግጭቶች ነበሩ። በዛ ላይ ወጥቼ እንድሰራ አትፈልግም፤ ስወጣ ትቀናለች። እኔ ደግሞ እዚህ ሀገር የመጣሁት ከነጻነቴ ባሻገር ራሴን ልቀይር ነው። የሰው እጅ እየጠበቅኩ መቀመጥ አልፈለግኩም። ስለዚህ ተለቃቀሰን ተለያየን እና ለተሻለ እድል ተመልሼ ወደ ናይሮቢ መጣሁ። ወደዚህ ከመጣሁ በኋላ የት እንዳለሁ አታውቅም ነበር፤ እኔም አልነገርኳትም። ከሰባት ወር በኋላ አፈላልጋ አገኘችኝ። ከዛም መሀላችን ፍቅር ስላለ በድጋሚ አብረን ሆንን። እኔም ትንሽ ስራ ሰርቼ ቤት ተከራይቼ ስለነበር አብረን መኖር ጀመርን።




አሁን የነበሩንን ችግሮች ፈተተን ብናገኝም ብናጣም አብረን ነን። ሁለታችንም እየሰራን፤ እናቷም ተቀብላን፤ ተመርቀን እየኖርን ነው። ብዙ ጊዜያችንን አብረን እናሳልፋለን። አንድ ልጅ አለን፤ ብቻዋን የምታሳድገው ልጅ ነበራት። አብረን ስንሆን ልጃችን ገና አንድ አመቱ ነበር፥ አሁን አራት አመት ሆኖታል። እሷ ስራ ስትሄድ እኔ እየዘዋወለሁ፤ እኔ ስሄድ እሷ ትዩዘዋለች ከልጅነቱ ስለሚያውቀኝ እንደ እናቱ ነው የሚያየኝ እና የሚወደኝ። ሲጠራኝም ʻማም" ብሎ ነው። እግዚአብሄር ካሰካ ደግሞ አንድ ልጅ ብንጨምር ደስ ይለናል። እሁዳችንን አብረን ቤተ ክርስቲያን በመሄድ እናሳልፋለን። ከምሳ በኋላ ደግሞ ፓርኮች እንሄዳለን ወይም ቤታችን ቡና አፍልተን የሀበሻ እና የኬንያ ምግብ በመስራት እና በመመገብ እናሳልፋለን። በጣም ነው የምንዋደደው፤ አልፎ አልፎ ግጭቶች አይጠፉም ግን ያለ ነው። እውነት ለመናገር የምበረታው በፍቅራችን፤ በልጃችን፤ በባለቤቴ፤ በእናቴ እና ሀይማኖቴ ነው። ከእናቴ ጋር አሁንም እንደዋወላለን፤ ኦርቶዶክስ ሀይማኖቴንም አጥብቄ ነው የያዝኩት።




> ❝ ነጻነቴ የመጣው ከመገለል፣ ከዝምታ እና ከትግል ጋር ነው... ግን ምንም ፀፀት የለዉም። ʻነጻʼ ብለው የጠሩኝ፣ ስድብ እንደሆነ አድርገው ነዉ... ነገር ግን ነጻነት ከምርጫዎቼ ሁሉ ጀግንነት ያለበት ነው።



“ ልጄን የቤት ስራውን በመስራት አግዘዋለዉ። ለራስ ፍቅር ስለመስጠት ኃያልነት ብዙ ጊዜ አስተምረዋለሁ።



“ በማይቀበለን ዓለም ውስጥ፣ የራሳችንን አስተማማኝ መጠለያ እንፈጥራለን። ቤት ማለት ቦታ አይደለም... እሷ ናት፣ እኛ ነን፣ ከምወደው ሰው ጋር የምወደውን እግር ኳስ መመልከት ነው።

## የወደፊት እቅድ እና አላማ

ወደፊት ቢዝነስ ልጀምር አስባለሁ፤ መታወቂያ ለማውጣት ፕሮሰስ ጀምሬያለሁ። ፀሄ ሲሳካ በእግሬ ቆምኩ እላለሁ። ስኬት የምለው ሰው መጠየቅ ሳቆም እና የሰው ፊት ከማየት አልፌ ቤተሰቤንና ሌሎችን የምረዳበት ደረጃ ስደርስ ነው። ከዛ በላይ ግን ትልቁን ስኬት አሳክቼዋለሁ ባይ ነኝ። ራሴን መቀበሌ ትልቁ ስኬቴ እንደሆነ ስለማምን ከምንም በላይ ያኮራኛል። ምክንያቱም ራሱን ያልተቀበለ ሰው እንኳን ለሌላ ለራሱም አይሆንም።

## መልእክት

ለወገኔ መንገር የምፈልገው መልእክት እንደኛ ምስኪን÷ ሩህሩህ እና አሳቢ ማህበረሰብ አለመኖሩን ነው። መገፋትን ስለምናውቅ ሰው አንገፋም። የኢትዮጵያ ህዝብ ፀሄንን እንዳያውቅ እፈልጋለሁ። በዛ ላይ እንደኛ ትንሽ ሆኖ መተባበርን፤ አንድነትን ቢማር ባይ ነኝ። እንደምሳሌ የምንሆን እንጂ በመጥፎ የምንፈረጅ አልነበርንም፤ ባይቀበሉን እንኳን ማንነታችንን ቢያከብሩልን ደስ ይለኛል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ላሉ የሀገሬ ልጆች ደግሞ በርቱ፤ አልታመማችሁም፤ ተፈጥራችን ነው፤ ሀጢያተኛም አይደላችሁም፤ እግዚአብሄር ይወደናል፤ እኛም ራሳችንን እንውደደው፤ እንቀበለው፤ በራስ መተማመን ይኑረን፤ በጽናት እንቆይ በሰው ፊት ቆመን የምንመሰክርበት ጊዜ ሩቅ አይደለም፤ በጎው ጊዜ እስኪመጣ መጥፎውን ጊዜ በአንድነት እየተባበርን እንለፈው ልላቸው እወዳለሁ።

በእምነታችን ጸሎት እናድርግ፤ ለሁሉም ጊዜ አለው፤ ለራስ የሚሰጥ ትግስት ያስፈልጋል፤ በከባዱ ሰአትም ምንም ብንሆን ተፈጥሮ መሆኑን አውቆ ራስን በጸጋ መቀበል፤ ፍቅር ጾታ ሀይማኖት እድሜ እንደሌለው ማወቁ መልካም ነው እላለሁ።



## ሄለን እና ግሬስ







> ግራ የሚያጋባኝ፤ መሀል ላይ የቆምኩበት ወይንም የሚያልፍ ስሜት አይደለም።

**ትርፋችን ግን እኔና አንቺ አብረን መሆናችን ነው።**

ዋነኛው ነገር ውሳኔ እና ራስን ተቀብሎ ለሚወዱት ሰው ታምኖ እና አምኖ መኖር ነው። እኔ ሄሉን ሳገኝ አለም ነው የሆነልኝ፤ ምክንያቱም ወስናለች። ወደኋላ የምታየው ነገር አልነበራትም።

## የማንነት መገለጫ

ሄለን፡ ለእኔ ማንነቴ ወይም መገለጫዬ ብዬ የምገልጸው የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነቴን ነው፤ የተቀበልኩት እና የምኮራበት ነገር ነው።

ግሬስ፡ ማንነቴን የምገልጸው ጥንቁቅ፤ ልዩ እና ውስጧ በትክክል ምን እንደሚፈልግ የምታውቅ ነኝ ብዬ ነው። ለእኔ ኩዊር መሆን ማለት ልክ ማንኛውም ተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ማንነቱን ፈልጎ እንዳላመጣው ሁሉ የኔም ኩዊር መሆን ተለማምጄ ያመጣሁት ሳይሆን ተፈጥሮዬ የሰጠኝ፤ ንጹህ ማንነት ነው።

ሄለን፡ አልዋሽም ከማንነቴ ጋር እታገል ነበር፥ በረኪና ለመጠጣት ያሰብኩበት ጊዜ ሁሉ ነበር። ማንነትን መቀበል ቀላል አልነበረም ከብዙ ነገር ጋር ነው የሚያፋልሰው፥ ለጉዳዩ በቂ ያልሆነ ግንዛቤ ስለነበረኝ በብዙ ጭንቀቶች እና ራስን መጥላት ውስጥ አልፌያለሁ። እያደግኩ ስመጣ እና ለስሜቴ እውቀት ሲኖረኝ፤ ራሴንና ተፈጥሮዬን ስቀበል ግን ትልቅ ለውጥ አምጥቻለሁ። ከምንም በላይ ግን ራሴን ስቀበል የአእምሮ እረፍት እና ሰላም እንዲሁም ለራሴ ፍቅር ኖሮኛል።


## ራስን ማወቅ እና ከትናንት የዛሬ ለውጥ

ግሬስ፡ ለሴት የተለየ ስሜት እንደኖረኝ ካወቅኩ በኋላ ከመንፈሳዊ ህይወቴ ጋር ይጋጭብኝ ነበር። ያለኝን ነገር ከሴቶች እና ከወንዶች ስሜት ጋር እያነጻጸርኩ ስሜቴን አጠናዋለሁ፤ መጽሀፍ ቅዱስ እያነበብኩ ሀጢያተኛ አለመሆኔን ለማረጋገጥ ደክሜያለሁ። ስለእኛ ማህበረሰብ በመመርመር እና ጽሁፎችን በማንበብ፤ ራሴን በማጥናት በብዙ መልኩ እኔነቴን አሻሽያለሁ። ስለዚህ ከተነሳሁበት መነሻ ሳየው ብዙ መንገድ መጥቻለሁ፤ ብዙ ለውጥ አለኝ።


ሄለን፡ ራሴን መቀበሌ ብዙ ዋጋ የከፈልኩበት እና ተፈጥሮዬ እንደሆነ አምኜ እስክቀበል ከራሴ የተቀየየምኩበት ስለሆነ ወደኋላ አልመለስም። አሁን ሙሉ በሙሉ ራሴን ተቀብያለሁ። ግራ የሚያጋባኝ፤ መሀል ላይ የቆምኩበት ወይንም የሚያልፍ ስሜት አይደለም፤ እርግጥ ነው! ያለሁበትን በታም ማንነቴንም ተቀብዬው አምኜው ነው ያለሁት።

ግሬስ፡ እንዳልኩት እስቤ ወስኜ የሆንኩት ነገር ነው። እናቴን እስከመተው አድርሶኛል። ምንም ወደኋላ የለውም።

ሄለን፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት እንደምወድ ያወቅኩት ሰባተኛ ክፍል እያለሁ ነው።። እጅ እወድ ነበር፤ የሚያምር እጅ ያላት ሴት ሳይ ደስ ይለኛል። አንዲት የምወዳት ልጅ ነበረች። እጇ በጣም ያምራል። በጓደኝነት ተቀራርበን አብረን አደግን። ቤትም አብረን እንሄድ ስለነበር ሁሉም የሚያውቋት ነበረች፤ ሃይስኩል ስጨርስ ከፍላጎቴ አንጻር ራሴን ልገታ እና ሳስተው ያልቻልኩበት ስለነበር ያኔ ስለራሴ በደንብ እርግጠኛ ሆኜ ነበር። ከዛ ግን ስለእሷ ምንም ሳላውቅ ትንሽ ፈጠንኩባት እና ፈራችና ገሸሽ አለች። ከዛ በኋላ እንኳን እኔም አረብ ሀገር ሄድኩ። ስለዚህ ራሴን ያወቅኩት ትንሽ ሆኜ ነው ማለት እችላለሁ። ራሴን በደንብ የተቀበልኩት ግን ሃያዎቹ ውስጥ ሆኜ ነው።




❝ በየማለዳው ይህንን መጽሐፍ የምከፍተው ሕይወት ቀላል ስለሆነች ሳይሆን፣ ነፍሴ ተስፋና ጥንካሬ ስለምትፈልግ ነው። – ግሬስ



❝ በቤታችን ውስጥ፣ ከሕያውና ከዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር ቃል እንማራለን፣ እንሰማዋለን፣ እንዲሁም እንመገበዋለን። እምነት የላችሁም ብለው ለሚያስቡ ሰዎች ሁሉ፦ ስንፈጥር እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነበረ፣ ዛሬም ከእኛ ጋር ይኖራል። – ሄለን

ግሬስ፡ ስራ ከጀመርኩ በኋላ አንድ ቀን ቢሮ ሆኜ ከድሮም ጀምሮ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ሲጨንቀኝ ከማማክራት አስተማሪዬ ጋር በቴክስት እያወራን ነበር። ለብዙ ነገር መልስ ስፈልግ የማገኛት ሴት እሷ ነች። ለአዲስ ነገር ክፍት ከመሆኗ በተጨማሪ መንፈሳዊ እና የበሰለች ነች። ብዙ ጊዜ አመዛዝና መሆን ያለበትን ትነግረኛለች ብዬ ስለማምን "የተመሳሳይ ፍቅር ውስጥ መግባቱ በሀይማኖት ከመዳን አንጻር እንዴት ይታያል?" ስላት በጣም ሰቀችና "በኢየሱስ በድጋሚ የተወለደች "የዳነች ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ" ነዋ የምትሆነው" ብላ አስደነቀችኝም አሳቀችኝም። ያኔ ትልቅ እረፍት አገኘሁ። ሀጢያት እንደሴለው እንደማንኛውም ፍቅር የኛም ፍቅር ፍቅር እንደሆነ አረጋገጠችልኝ። እየፈራሁ "እኔ እኮ እንደዛ ነኝ" ስላትም ብዙ ሳትደነግጥ የሔለንን ፎቶ ፕሮፋይል ካደረግኩበት ቴሌግራም ላይ አምጥታ "እሷ ነች?" ብላ ስትጠይቀኝ "አዎ" አልኳት፥። ያውም ሁሌም ቻው ስንባባል ከንፈሯን እስማት ነበር ግን ከሁሉም ጋር የማደርገው ይመስላት ስለነበር አልጠረጠረችም። አብሬያቸው የነበርኳቸውን ወንዶች ስለምታውቅ "ወንዶቹስ?" ብላ ስትጠይቀኝ ሞክሬ እንዳልቻልኩ ማንነቴም እንዳልሆነ ነገርኳት። እስካሁን እናወራለን፤ ጥሩ ጓደኛዬም መካሪዬም ነች።

ሔለን፡ ራስን ለመቀበል መጀመሪያ መታረቅ ያለብሽ ከፈጣሪሽ ጋር ነው። ከሱ ጋር ከታረቅሽ ከራስሽ ጋር መታረቅ አይከብድም። ከራስሽ ጋር ከተስማማሽ ደግሞ ከቤተሰብም ሆነ ከማህበረሰብ የሚመጣ ተጽእኖ ከአቋምሽ ዝቅ አያደርግሽም ምክንያቱም መሰረትሽ አምላክሽ ነውና!

እውነት ለመናገር በዚህ ዙሪያ ብቸኛ ነበርኩ። የማዋየው ሰው አልነበረኝም፤አብረውኝ ያሉ ሰዎች ከጥርጣሬ የተነሳ አልፎ አልፎ ጥያቄዎችን ይጠይቁኝ ነበር እንጂ ማንም ስለእኔ በግልጽ የሚያውቅም እኔም ደፍሬ የማዋየውም አልነበረም። በነጻነት ማውራት የጀመርኩት ግሬስን ካገኘሁ በኋላ ነው። መሰረቴ ሙስሊም ነው። ቁርአን የቀራሁ ሰው ነኝ እና በፊት ለአምላኬ ላዋዩ አጸልዩና "ለነገሩ አንተም አትቀበለኝም" ብዬ ከእሱም ጋር እጣላ ነበር። ከዛ ግን "እሱ አዩደል እንዴ የፈጠረኝ በራሱ ስራ የሚያፍር አይመስለኝም" ብዬ ራሴን አጽናና እና አረጋጋለሁ።

ያው እድገቴ ከብዙ ፕሮቴስታንት ጓደኞቼ ጋር ስለነበር ከልጅነቴም ብዙ መዝሙር አዳምጥ ነበር። በዛ ውስጥ አልፌ ደግሞ ጌታ ግሬስን ላከልኝ እና ቸርች ውሰጂኝ ማለት ጀመርኩ። ረመዳን ሲመጣ ደግሞ እስልምናን ትቼ መተው ያቀተኝ ስለነበር እጾም ነበር። እዚህ ከመጣን በኋላ ግን አንዱ ጓደኛችን ታሞ ልንጠይቅ ሄደን እንዳጋጣሚ ሁሉም ፕሮቴስታንት ስለነበሩ ተመቻቸው። እዛው አፈኑኝ (ሳቅ) ጸለዩልኝ እና ጌታን እንድቀበል ሆንኩ። በርግጥ እኔም አልወሰንኩም እንጂ ልቤ አጋድሎ ነበር። ግሬስ ደግሞ እምነቷ ላይ ጠንካራ ስለሆነች ወደ እሷ መራችኝ፤ ይኸው አሁን የደህንነት ትምህርት ጀምሬያለሁ።

> "እሱ አዩደል እንዴ የፈጠረኝ በራሱ ስራ የሚያፍር አይመስለኝም"
>
> -ሔለን



“ እውነቱን ለመናገር፣ አብዛኛውን ቀናችንን የምናሳልፈው ቤት ውስጥ ነው። በስልካችን ፊልም እናያለን።  ጊዜ ለማሳለፍ ይረዳናል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፊልሙን ረስተን ፍቅር እንሰራለን። – ሄለን




“ ሁሌም ቢኖረኝ የምመኘውና ቤቴ ዉስጥ ማጣት የማልፈልገው ነገር ቢኖር ብስኩት እና ቸኮሌት ነዉ። ብር ሲኖር የምገዛው የመጀመሪያ አስቤዛ ነው። – ግሬስ

## ከሀገር የመውጣት ሀሳብ

ሄለን፡ እኔ እንኳን ከሀገር ለመውጣት ያሰብኩበት ጊዜ አልነበረም ብለሽ ነው? ግን የማልረሳው አጋጣሚ ግሬስን ከማወቄ በፊት የማውቃት ከደቡብ አፍሪካ ከመጣች ልጅ ጋር ነበርኩ። አንድ ማታ ሆቴል ይዘን ልናድር እየገባን የዛ አካበቢ ልጆች ተከታትለው ስሜን እየጠሩ መጡ። “ከዚችጋ ምን ትሰሪያለሽ? እቺ እኮ እንደዚህ ናት” እያሉ ውስጥ ገብተን ዘግተንባቸው ራሱ የረበሹን አይረሳኝም። በዚህ ልክ ማንም ይከታተለኛል ብዬ አላውቅም ነበር÷ የሆቴሉ ሀላፊ ነው “ለምንድን ነው ሆቴሌን የምትበጠብጡት?” ብሎ ያባረረልን። እስከሌሊት ድረስ ቆመው “ውጡ!” እያሉ ሲጩሁ ቆይተው በመጨረሻም ሀላፊው አስፈራርቷቸው ሄዱ። የዛኔ ልጅቷ ግራ ገብቷት ጭራሽ ፖሊስ ጋር ልደውል ብላ ነበር። እኔ ደግሞ በእና ሀገር የኛ ጉዳዩ ህግ የሚፈቅደው እንዳልሆነ ስለማውቅ የፖሊስ ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ አይደለም ብዬ አስተውኳት። የማልረሳው እና ሀገሬ ላይ እንደማልቆይ የወሰንኩበት ጊዜ ነው።

ግሬስ፡ የወሰንኩት እሷ ከሀገር ወጥታ አረብ ሀገር በነበረች ወቅት ነው። ስትመለስ አብረን የምንሆንበት ቦታ ስላልነበረን እኔ ደግሞ የምኖረው ቤተሰቦቼ እጅግ ወግ አጥባቂ ስለነበሩ አራት ተሰብስበን አብረን የምንበላ፤ አንዱ ሰው ካመሸ የሚጠበቅበት፤ አስር ጊዜ የሚደወልበት ቤት ስለሆነ ውጪ መውጣት እና ማምሸት የማይታሰብ ነበር። የነበረው አማራጭ የእሷ እና ጋር መሆን ስለነበር እና ቤት አረፈች። እኔ ቀን ስራ ስሄድ ቤት መዋል ስለሚደብራት አብረን ወጥተን ስራ እንሄድና እሷ ውጪ ስትንቀዋለል ትውላለች። እኔ ስራ ቦታ ሆኜ ውጪ መሆኗን ሳስብ ጭንቀት ሲገለኝ ይደርስ ነበር። ውዝግብግብ ማለት ሆነ እጣፈንታችን። ለሰከንድ መለያየት አንፈልግም ነበር፤ ሁሉ ነገራችን የሚፈላለግ ነን። ሰውነታችን፤ መንፈሳችን፤ ጸጉራችን ሳይቀር አንድ ላይ መሆን ይፈልጋል። ያለው ሁኔታ ደግሞ በተቃራኒ አብሮ ለመሆን አልተመቸም። ቤተሰብም ጥያቄ መፍጠር ጀመረ፤ የመጀመሪያ ልጅ እንደመሆኔ መጠን የትዳር ጉዳዩ ይነሳል። በዙሪያዬ ደግሞ አከሊት እንጂ አከሌ አልነበረም። አነሱም እያንዳንዱን እርምጃዬን የውቁ ስለነበር አካባቢዬ አንድም አከሌ እንደሌለ የውቃሉ እና ሁኔታችን ጥያቄ መፍጠር ጀመረ። በነሱ ቁጥጥር ምንም ህይወት መመስረት አልችልም ነበር። እዚህ ስመጣ ራሱ ነገ ካናዳ ልገባ ነው ብዬ ዋሽቼ እንጂ አፍሪካ ሀገር መሆኑን ቢያውቁ እናቴም ትሞትብኝ ነበር። “ሬሳዬን ተራምደሽ ሂጂ” ብላኝ ከኬንያ ካናዳ እንደሚቀል አሳምኛት ነው የመጣሁት።

አንድ ላይ ለመሆን ስንል ዋጋ ከፈልን፤ ቁጭ ብለን አውርተን ወሰንን። የመጨረሻ ቀን እንዲህ አልኳት። “ሄሉ አሁን ወስነናል÷ መረጃ አግኝተናል፤ ፕሮሰሱ አንድ አመትም አስር አመትም ሊፈጅ ይችላል። ልንቸገርም፤ ልንራብም፤ ልንታመምም፤ ልንሞትም እንችላለን። ትርፋችን ግን እኔና አንቺ አብረን መሆናችን ነው።”

## ኩዊርነት በኬንያ

ግሬስ፡ በማንነታችን የተነሳ ችግር ያጋጠመን ኤርፖርት ላይ ይመስለኛል። ሻንጣችን ተይዞ ስለነበር አንዷ ሰራተኛ በጥያቄ አፋጠጠችን፤ “ወይ ወደውጭ ለመውጣት ነው ወይ ሁለታችሁ የሆነ ግንኙነት አላችሁ” ብላ አስጨነቀችን። ደግሞ እኔ ቀድሜ አልፌያት ገብቼ እሷ ስትያዝ ነው የተመለስኩት፤ “እንዴት ገባችሁ?” ብለው የሆነ ቤት ውስጥ አስገብተው ከነሻንጣችን ቆለፉብን። የያዛችሁትን ወረቀት አሳዩን ተባልን፤ ደግሞ ኩዊር ነክ ጽሁፎችን ይዘን ስለነበር “ዛሬ አለቀልን” ብለን በጣም ተሳቀቅን÷ እግዚአብሄር ነው ጣልቃ ገብቶ ሽፍንፍን አድርጎ ወደሌላ ሰው የወሰደን። እሱ እንደመጀመሪያዋ ብዙ ሳያካብድ አሳለፈን። እድለኞች ነበርን ማለት እችላለሁ።

ናይሮቢ እንደደረስን ሹፌር አናግረን ዳውን ታውን ሄድን፥ ሹፌሩ ያለን መስሎት ይሁን ወይ አዲስ እንደሆንን አውቆ በውድ አሳፈረን። በእርግጥ ካለፈ በኋላ ነው የገባን። የሱ ሳይበቃው በአምስት ሺህ ሽልንግ ክፍል አሲያዘን። ማንንም ስለማናውቅ ዋጋው ውድ ይሁን ርካሽ የምንጠይቀው ሰው እንኳን አልነበረም። የምናውቀው የቀረን አምስት ሳንቲም እንኳ እንደሌለን ነው። ምግብ የበላነውም ስንነሳ ቁርስ ላይ ነበር፤ ባዶ ሆዳችንን ነው የዋልነው። ከወረድንበት ቦታ ባለታክሲዎቹን ሀበሻ ያለበት ሰፈር ውሰዱን ስንላቸው አንድ ሺህ አምስት መቶ ሽልንግ ጠሩልን፥ ሰላሳ ሽልንግ እንኳ የማያወጣ መንገድ ነው ግን አዲስ መሆናችንን አውቀው ሊያታሉን ሞከሩ። ገንዘቡ ስላልነበረን ትተናቸው ሀበሻ ካገኘን ብለን መንገድ ላይ ዝም ብለን መፈለግ ጀመርን። መንገድ ላይ እንኳን ብናድር ብለን የያዝናት አንድ አንሶላ ነበረች፤ ማደሪያ ካጣን እሷን ለብሰን እንተኛለን እስከዛው ግን ዞር ዞር ብለን ሀበሾች እንፈልግ ተባብለን መፈለግ ጀመርን። እንደአጋጣሚ ሁለት ወንድ ሀበሾች ስናገኝ በደስታ አስቀመን ቦታ እንዲመሩን ጠየቅናቸው፥ “እንዴት በዚህ ጊዜ መጣችሁ? አሁን እኮ ምዝገባ የለም” ብለው መጥፎ ዜና ቢነግሩንም እንዴ መጥተናል ምን ማድረግ እንችላለን ብለን ከቻሉ ሀበሻ ወዳለበት ሰፈር እንዲመሩን ጠየቅናቸው። ከዛም ሶስት መቶ ሺልንግ ከፍለው ሀበሻ ሰፈር ጃሞሪ ወይ መድሀኒያለም ቤተክርስቲያን ብላችሁ ሂዱ ውህና ማደሪያ ይሰጧችኋል ብለው አሳፈሩን።

ጃሞሪ ስንደርስ ነጠላ የለበሱ ሰዎች ማየት ስንጀምር ሀገራችን ያለን ያህል ደስ አለን። በአማርኛ ስሙ የተጻፈበት ሆቴል ደረስን እና ገብተን ቁጭ አልን። ሄሉ ከእኔ ትንሽ ፈጠን ስለምትል ጨዋታ ጀመረች፤ የሆንነውን ካጫወተቻቸው በኋላ ካኩማ ካምፕ የት እንደሚገኝ ጠየቀቻቸው። ከሀገራችን ስንነሳ ስራ ካገኘን እንሰራለን ካላገኘን ደግሞ ካኩማ（የስደተኛ መጠለያ）እንገባለን ተባብለን ነው የመጣነው።

ሄለን፡ እዛ ከሚያዳምጡን ውስጥ አንዷ “ምን ሲደረግ እናንተን የመሰሰሉ ልጆች ካኩማ ይገባሉ?” አለችን። ያኔ ወዘሞች ነበርን፤ ገና ከቤት እየወጣን ስለነበር አልጠወለግንም ነበር።（ሳቅ）“እዚህ እኔጋ ስራ ትጀምራላችሁ” ስትለን አላመንናትም። ‘ባር ልከፍት ስለሆነ አንዳችሁ በአስተናጋጅነት ትገባላችሁ፥ ለአንዳችሁ ደግሞ ሌላ ቦታ ይፈለጋል” አለች። እግዜር ረዳን አልን።



ግሬስ፡ ያን እለት ማደሪያ ሲፈለግልን አንድ እሱ ጋር ታድራላችሁ የተባልን የፈጣጠነ ባለጌ ሰው አጋጠመን። መቼም የአዲስአበባ ልጅ የሀገር ሰው ነው ብለን እሺ አልን፤ እሱ ግን ተንቀለቀለ። ሲያስቸግረን ውሎ አይመሽ የለ መሸና ማታ ላይ ቤቱ ይዞን ሄደ። "ሻወር ውሰዱ÷ አንቺ በቃ ነገ ስራ ትጀምሪያለሽ" ተባልኩ። የሄሉ ደግሞ እግዜር ያውቃል አለን። ከዛ ማታ ደስታውን እናክብር መጠጥ ካልጠጣን ብሎ የሚጠጣ ከፈተ። እኛም ሰው ቤት ነን በዛ ላይ በአንድ ቀን ስራ ስለተገኘልን እሺ ብለን በመጠኑ መጠጣት ጀመርን። እኔ ግን ትንሽ አወራሁ እና ባለሁበት እንቅልፍ ጣለኝ። በጣም ደክሞኝ ስለነበር አልቻልኩም፤ ሄሉ ደግሞ መቼም ሰው ቁጭ አድርጎ አይተኛም ብላ በዩሉኝታ ትንሽ ስታጫውተው አመሸች። ገና መጠጡን ስንጀምር ግን "አንድ ነገር እንኳ ቢፈጠር እንሰማማ ራሳችንን ጥለን እንዳንተኛ÷ እንጠባበቅ" ተባብለናል።

ሄለን፡ ከዛ ሰውየው እየተቀየረ መጣ፤ መንካት ፈለገ። ለሀገሩም ለቤቱም እንግዳ ነን፤ ያገኘነውንም እድል አላበላሸውም ብዬ ላባብለው ሞከርኩ። ተው አይሆንም ብለው ጭራሽ ፒጃማዬን ይጎተት ጀመረ። ከዛ ግሬስ ድንገት ብድግ አለች! እንጣጥ ብላ አንገቱን በክርናዷ አነቀችው። ጠጥቶ ስለበር አቅም አልነበረውም እግዜር ይስጠው! እኔም እሷን ሳይ ወኔዬ መጣ እና ተጋገልን። "አንተን ገለንህ እስር ቤት እንማቅቃታለን እንጂ ምንም አይመጣም" አልነው። ስካሩ ሁሉ በድንጋጤ ለቀቀው። "እሺ እሺ እሺ" አለ!

ግሬስ፡ ከዛማ እኤም ማስቴን ጠቅልዬ ተኛሁ፤ አይነጋ የለ ነጋ። የዛን እለት ማታ ስራ ልጀምር ስል ሄሉን ብቻዋን ሰውዬው ጋር እንደማልተዋት ለካላፊዋ ነገርኳት። "ካልሆነ ስራው ይቀራል አልኩ" አታስቢ ብላ የእሷ ሴት ጓደኛ ቤት አሳደረቻት። ለመጀመሪያ ጊዜ ለየብቻ አደርን ማለት ነው። እኔ በጀመርኩ በሁለተኛ ቀን ሄሉ እዛው ቤት ቀን ቀን ቡና ጀመረች። እግዚአብሄር ሲወደን አንድ ላይ አደረገን፤ ግን ያው ትግሉ አያልቅም የኔ ስራ ማታ ማታ ስለሆነ ወንዶቹ እያስቸገሩ አላሰራ አሉኝ። "አንቺ ማነሽ ከሌሎቹ በምን ትለያለሽ?" እያሉ ከኔ ጋር እልህ ተጋቡ። እኔም ሀይለኛ ስለሆንኩ ሌላው ስቆ የሚያልፈውን ማለፍ አቃተኝ። ሴትየዋም ትከላከልልኛለች ግን አስቸጋሪ ሆነ። ይባስ ብሎ እዛው አብሮኝ በሚሰራ ወንድ ባሰ። አንድ ማታ ድርቅ ብሎ "ካልሳምሽኝ" አለ። እኔም ደግሞ "ምንም ይቀራል እንጂ አልስምህም" አልኩ÷ "እንደዛ ከሆነ ስራሽን አበላሻለሁ" አለኝ አፉን ሞልቶ። "እንደፈለግክ" አልኩት። እንዳለውም ስራ በጀመርኩ በሁለት ወሬ በሶስተኛው ቀን ባለቤቷ ጠርታ ደሞዜን ሰጠችኝና "ተሰናብተሻል" አለችኝ። የባለቤቷ ቀኝ እጅ ስለሆነ ተሰሚነት አለው፤ በመጀመሪያ ወር ቲፕ ከገቢ በላይ ታገኛለች ብለው ደሞዝ ቀንሰውብኝ ነበር፤ በቀጣይ ደግሞ በዚህ ምክንያት አሰናበቱኝ።

ሄለን፡ ከዛ በኋላ የምንኖረው በአንድ ሰው ገቢ ብቻ ሆነ። በምናገኘው ደሞዝ ቤት ኪራይ አናቱ ላይ ነው የምንከፍለው፤ ያውም ሳሎኑ የጋራ የሆነ ቤት ውስጥ እየኖርን። ለሌላ ነገር ገቢ ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ሆነ። ከዛ በኋላም ግሬስ ሁለት ተመሳሳይ ስራ አግኝታ ነበር፤ ነገር ግን ወንዶች በትንኮሳ አላሰራ ይሏታል፤ ትተወዋለች። ያው እንኳን ቆንጆ ሆነሽ ሴት በመሆንሽ ብቻ ትንኮሳ አይቀርም አይደል? በዛ ላይ አንድ ላይ መሆን አልቻልንም፤ አንድነታችንን መተሳሰባችንን አጠፉብን። መያያዝ፣ መጎራረስ፣ አብረን መብላት እስካንችል እየተከታተሉ ግራ አጋቡን። ለየብቻ መብላት አይደለም ሳንጎራረስ ራሱ በልተን የማናውቅ ልጆች አሳቀቁን። በቃ ትንሿ ኢትዮጰያ ሆኑብን፤ ነጻነታችንንም ፍቅራችንንም ሰላም ነሱት÷ "እንዴት በዚህ ልክ ልትተሳሰቡ ትችላላችሁ? በዚህ ልክ ምን ስለሆናችሁ?" ብለው ከአከራያችን ጀምሮ ይከታተሉን ጀመር÷ በተቃራኒው ደግሞ ከወንድ ጋር የማይገናኙ ጨዋ የአዲስ አበባ ልጆች ብለው የሚያመሰግኑንም ነበሩ። የነዛ ትኩረት ግን ባሰ፤ መላ ስራቸው እኛን መከታተል ብቻ ሆነ። አከራያችን በእኛ መተሳሰብ በጣም ትቀና ነበር፤ ታለቅስ ሁሉ ነበር። ከዛ ግን ከቤት ልቀቁ ብላ ነው ያስወጣችን። በዛ ላይ ትተው አይተውሽም፤ ስላንቺ ማጥናት ይፈልጋሉ። የአዲስ አበባ ልጅ ናት ከተባለ "የት ሰፈር? የት ትምህርት ቤት ሄድሽ? ማንን ታውቂያለሽ?" ብለው ሲያጣሩ ይሞክራሉ።



“ አንድ አይነት ጫማና ልብስ የምፈልገውና በጣም የምወደው የፍቅር ስሜቴን የሚገልጽልኝ ነገር ነው። መተሳሰብንና አንድነትን ያሳየኛል፣ ነፃነትን ፣ መተማመን ከፍቅሬ ጋር ጥሩ ግንኙነትና በጣም ቅርብ የሆነ ቤተሰባዊነት እንዲሰማኝ ያደርገኛል – ሄለን



“ ሰው እናቱ እና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል እንደሚል ቃሉ፤ እኔ እና ባለቤቴም በአካልና በመንፈስ በሃሳብ ልክ እንዲህ ተጣብቀናል።  ሳፈቅራት ልክ የለኝም 🥰 – ግሬስ


> "አንድ ነገር እንኳ በፈጠር እንሰማማ ራሳችንን ጥለን እንዳንተኛ፥ እንጠባበቅ"
>
> – ግሬስ

## የመጠለያ ህይወት

ግሬስ፡ ያው የተከራየሽውን ቤት ለመልቀቅ አንድ ወር ሲቀርሽ መናገር አለብሽ። የሆነ የመጠለያ ቦታ ፕሮሰስ ስንጀምር በቀጣዩ ወር እንደምንለቅ ለአከራያችን ነግረናት ነበር። የመጨረሻ ቀን አርፍደን ተኝተን በድንገት በራችን በሀይል ተደበደበ። “ምን መጣ?” ብለን በርግገን ስንነሳ አከራያችን “ኑ ውጡ እናንተ ድሮውንም ሴዝቢያኖች እንደሆናችሁ ታውቆባችኋል” እያለች መጮህ ጀመረች። በጣም ፈርተን ነበር። ያለንን እቃ ይዘን በፍጥነት ከቦታው ተሰውረን... ወደ መጠለያ ሄደን ገባን። እዛ ደግሞ በደንብ ለሌብነት የተደራጀ ቦታ እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብንም። በኛ ስም ለዛኛ የሚበሉ ሌቦች ለእኛ ግን ቁራሽ ዳቦ እንኳን የማይሰጡ ሆዳሞች ነበሩ። መቼስ ቤት ካገኘን ምግብ ከየትም አንበላለን ብለን ይሁን አልን። እንዳጋጣሚ ድርጅት የራስ ማደራጀት ፕሮሰስም ጀምረን ነበር እና በመጀመሪያ ዙር እድል ቀንቶን ያለ መታወቂያ ብር ሰጡን። በዛ ብር የቡና ቢዝነስ ጀመርን። ፍቃድ ባይኖረንም በእግዚአብሄር ፍቃድ እየሰራን መኖር ጀመርን።

ሄለን፡ መጠለያው ገና ስንገባ “ምግብ፣ ዋይፋይ ሁሉ ነገር አለ የተሟላ ነው” ተብለን ነበር። ግን እንኳን ምግብ ሲኖር ቂጣ የምንጋግርበት ዱቄት እንኳን ከኪሳችን ሰማኒያ ሽልንግ እያወጣን ነበር የምንገዛው። ያ ብር ባይመጣ ደግሞ በርሀብ እንሞት ነበር። ባዶ ቤት ነው የተረከብነው፥ ባዶ! ግን መንገድ ከመውደቅ በስንት ጣእሙ! አራት ወር በዛ ሁኔታ ከቆየን በኋላ ጭራሽ የመጠለያው ባለቤት የአክስት ልጅ እኛ ጋር ሩም ሜት ሆና ትኖር ስለነበር ባለቤቷ የስፖንሰሮቹ ብር አልበቃ ብሏት “ፈንድ ስለቀመ በወር ስድስት ስድስት መቶ ሺልንግ እያዋጣችሁ ሺህ ሁለት መቶ ሽልንግ ለእሷ ስጡልኝ” አለችን። እምቢ እንዳንል እንዳንባረር ፈራን። “ከየት አምጥተን?” እንዳንል ቢዝነሳችንን ታውቃለች እና እንደፈረደብን ሺህ ሁለት መቶ ብር በየወሩ ለእነሱ መቁረጥ ጀመርን። በዚህ ቢበቃ ጥሩ ነበር፤ ጭራሽ ቀጣዩን ሁለት ወራቶች የምግብ እና የኪራይ ሲገርመን መብራትም ተቆርጦ በርም እየተቆለፈብን የሚከፍትልን አጥተን በግምብ እየዘለልን ቤት መግባት ጀመርን። የቤታችንን የውስጥ በር በድጋሚ በሌላ ቁልፍ እንዳይዘጋ ብለን እንጨት እየወተፍንበት በጨለማ ያለኢንተርኔት ስልካችንን ስራ ቦታ ቻርጅ እያደረግን እንደምንም ቆየን። የሚገርምሽ ግቢው ደግሞ ሳር ብቻ ነውና እባብ ሁሉ ነበር፤ ሲነድፈንም ያለበት እለት ነበር። ሁሉም ነገር ተበታትኖ ስለነበርና ግቢው የማያስተካክለው ስላልነበር ጨካ ሆኖ ሰው የሌለበት ያለመብራት አንድ ጀሪካን ውሃ አምሳ ሽልንግ እየገዛን ቆየን።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ከሼልተር ወጥተን ደግሞ ሌላ ቦታ ገባን። አንድ ወር እዛ ቤት የእረፍትም የጭንቀትም ጊዜ አሳለፍን። እረፍቱ ጥሩ የተከለለ ቤት ማግኘታችን ሲሆን ጭንቀቱ ደግሞ ስራ ዘግተን ስለመጣን ገቢ አልነበረንም።




❝ ይሄን ማለት የፈለኩት እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ እኛም ደህንነታችንን ማግኘት፣ በነጻነት ማውራት፣ መናገር፣ ክብራችን መጠበቅ፣ እኩል መታየት እንዲሁም ያለፍርሃት መኖር እንደሚገባን ለማሳየት ነው። – ሄለን




❝ ኢትዮጵያዊ ነኝ። ኩዊር ነኝ። ደግሞ የተወለድኩ ክርስቲያን ነኝ። ሦስቱንም በኩራት እናገራለሁ። ❤️🏳️‍🌈🇪🇹 በእጄ ያለው ፓስፖርት ዜግነቴን ያሳያል፤ በልቤ ያለው ማንነት ደግሞ ማን እንደሆንኩ ይናገራል። ማንነቴን የሚደግፍ የሚቀበል ማህበረሰብ ባይኖርም እኔ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ። ኢትዮጵያዊ መሆኔን እና ራሴን በእውነት መውደዴን እና ማንነቴን ተቀብዬ መኖሬን ማንም ሊነጥቀኝ አይችልም። አንድ ቀን ሁሉም ሰው የማንነቱን እውነት ሳይፈራ ለመኖር የሚችልበት ምቹ ኢትዮጵያን ላይ እጓጓለሁ። – ግሬስ

ሰው የሌለበት ቦታ ቡና አዩታሰብም። አብዛኛው የዛው ሀገር ሰው ብቻ ስለሆነ ስራ የለም። የሚገርመው ደግሞ በተቃራኒው ለማህበረሰባችን ጥሩ የሚመች ቦታ ነበር። ነጻነታችንን ስናገኝ ስራ ደሞ ጠፋ። ያሉት ሀበሾች በቁጥር አስር ራሱ አዩሞሉም። ስለዚህ መንገዳችንን መቀየር ነበረብን።

## ስደት እና ፍቅር

ሄለን፡ በመስረም 26 2021 ኢንስታግራም ላዩ ነው ማውራት የጀመርነው። ፕሮፋዩሏ የእኛ ባንዲራ ስለነበር በውስጥ "ሃዩ" አልኳት እሷም ወዲያው መለሰችልኝ። ማውራት ጀመርን። ፎቶ በስናፕቻት ስልክላት "ትክክለኛ ፊትሽን ነው ማየት የምፈልገው?" ብላኝ ላኩላት፥ የሷን ፎቶ ስትልክልኝ ግን ማመን አልቻልኩም። በጣም ቆንጆ ነች። "ጌታ ሆዩ እርዳኝ" አልኩ።

ግሬስ፡ ያን ቀን ትዝ ዩለኛል ጸጉር ቤት ነበርኩ። "በቃ አሁን ሚስቴን አገኘሁ" አልኩ። ያለሁት ውጪ ነው ስትለኝ ብቻ ትንሽ ቅር አለኝ፥ ማውራታችንን ግን ቀጠልን። ሰባት ወራት ያህል ጧትም ማታም አወራን። ስትመጣ የጠበቅኩት ትልቅ ሴት ነበር። እሷም እንደነገረችሽ አላመነችኝም ተሽከረከረችኝ። (ሳቅ) ያኑ ለት በራሳችን እና በእግዚአብሄር ፊት ቃል ተገባባን።

ሄለን፡ በመሀል በጣም ከመነፋፈቃችን የተነሳ እኔ በመጣሁበት ኤጀንሲ እሷን ወደአለሁበት ላመጣት ሞክሬም ነበር። ከዛ ግን ሰዩሰካ ሲቀር አላስቻለኝም፤ አመት ያህል እንኳን አልቆየሁም ኮንትራቴን ሳልጨርስ ተመለስኩ። ኗደኞቼም "ቆንጆ እና ታማኝ ልጅ አግኝተሻል ለምን ቀለበት አታስሩም?" ሲሉኝ በነሱ አገዛ ፕሮግራም አዘጋጀን። እሷም መጽሀፍ ቅዱስ እኔም ቁርአን ዩዘን እንደመጣሁ ቀለበት አደረግን። እሷ እንደውም ቤተሰቦቿ ጋር ጥያቄ ፈጠረባት። "እስከዛሬ ቀለበት አድርገሽ የማታውቂውን ዛሬ ከየት አመጣሽ?" ሲሏት ከመጨቃጨቅ ብላ አውልቃ አስቀመጠችው። እኔም ያረፍኩት ቤተሰቦቼ ጋር ነበርና እነሱ ደግሞ እንደሚታወቀው ከባድ ስለነበሩ አብረን የምንሆንባት ሰአት ማታ ስንተኛ ብቻ ነበረች። ከመተኛ ሰአት በፊት እንኳን መኝታ ቤት አንገባም ነበር። ቀን ቀን ደግሞ እሷ ስራ ስትሄድ አብሬያት እወጣና እስክትጨርስ ድረስ ስራዬ ውጪ መንጎማለል ነበር። ማታ ተያዩዘን ቤት እንገባለን በእንዲህ አዩነት ሁኔታ አንድ ወር ያህል ቆዩተን መመለሻዬ ከተባለው ቀን አለፈ። ቤተሰቦቼ ከውጭ የመጣሁ ኗደኛዋ እንደሆንኩ ተመልሼ እንደምሄድ ነው የሚያውቁት፤ የኔም ቤተሰቦች ተመልሰሽ ካልሄድሽ የመጨረሻችን ነው አሉኝ። ያኔ ደግሞ ፕሮፋዩል የእሷን ፎቶ አደርግ ስለነበር፤ እህቴ "ደግሞ ከየት ያመጣሻት ነች እቺ?" ትለኛለች። "ቸርች የማውቃት ናት" ስላት ሰዩዋጥላት ታልፈኛለች። በዚህ ምክንያት በልቤ ብሰቅላት ዩሻላል ብዬ ፎቶዋን መስቀል ተውኩ። (ሳቅ)

እመለሰለሁ ካልኩበት ጊዜ ሲያልፍ እህቷ መጠራጠር ጀመረች። እና ግን መለያየት ከበደን በጣም ስቃዩ ሆነብን፤ የሆነ ቀን ግን "ወዩ ሂጂ ወዩ ወስነሽ ቅሪ" አለችኝ። በቃ አልሄድም ብዬ ወሰንኩ እና ሙሉ በሙሉ እነሱ ቤት ገባሁ። ከዛ ግን የሷም ቤተሰቦች አላስቀምጥ አሉን። መቼ እንደምመለስ የሁሉም ሰው ጥያቄ ሆነ። ስለዚህ አዲስ ፕሮሰስ ጀምሬ በአስር ቀን ውስጥ አልቆልኝ ልሄድ ተነሳሁ። እሷም እንደፈረደባት ልትሸኘኝ ኤርፖርት መጣች። ውስጥ ድረስ ገብቼ መሄድ አቃተኝ፥፤ ሁለት ጊዜ ወጣሁ። በቃ አልቻልኩም፤ መለያየት አቃተን። በሶስተኛው ግን "ወስኒ አታድከሚኝ!" አለችኝ። ያኔ ቆርጬ ሄድኩ፤ ግን አንድ ወርም በስርአት አልቆየሁም። ትኬት ላከችልኝ ተመለስኩ። ቤትም "አመመኝ አልተመቸኝም" አልኳቸው። ሀገራችን አንድ ላዩ ውጪ ደግሞ ተለያዩተን መኖር እንደማንችል ሲገባን ወደኬንያ አንድ ላዩ ለመሰደድ ወሰንን።



“ እርግቦች እና እኔ.. እዚህ እርግቦች ሳይ ድሮ ኢትዮጵያ እያለሁ የማረባቸውን የራሴን እርግቦች ያስታውሱኛል:: ቀለማቸዉ፣ ሲበሩ ማየት፣ ድምጻቸውን መስማት ያስደስተኛል። – ሄለን



“ ከጓደኞቻችን አንዱ ቤተሰቦቹን ለመጠየቅ ወደ ኢትዮጵያ ዶ ነበር፤ እኔ ያንን ማድረግ ስለማልችል አዝኜ ነበር። ጓደኞቼንና ቤተሰቦቼን ባያቸዉ በጣም ደስ ይለኝ ነበር። – ግሬስ

ግሬስ፡ እኔ ሄሉን የወደድኳት ከጥፍሬ ጫፍ እስከ ጸጉሬ ጫፍ ነው። ይህን ሁሉ መከራ ስናይ እና በዚህ ሁሉ ውስጥ ስናልፍ የበለጠ እንድወዳት እና እንድንጠነክር ነው ያደረገን፥ ገና ስንነሳም ነግሬያታለሁ። “እኔና አንቺን ሊያለያዩን የሚችሉ ብዙ ፈተናዎች ይገጥሙናል፤ በጣም ከባድ ጊዜ ሊመጣ ይችላል። ግን ከኔ ጋ መንገድ የምትጀምሪው እኔነቴን ከወደድሽ ነው” ብዬ ተነጋግረን፣ ተማምነን ነው የወሰንነው። ለሚመጣው ትግል ሁሉ ዝግጁ ነበርን። አንዳንዴ እንስቃለን፤ አንዳንዴ እናለቅሳለን። ዋናው ሁሌም አብረን መሆናችን ነው።

ሄለን፡ ለእኔ ከምንም በላይ እሷን አገናኝቶኛል! ምንም ነገር ለማድረግ ዝግጁ ነበርኩ። አሁንም ድረስ ያ ስሜት ሰይቀዘቅዝ አለ፤ ፍቅራችንን እግዚአብሄር ይጠብቅልን።


ግሬስ፡ ከብዙ እንግልት በሗላ አዲስ ሰፈር ገባን፤ ኑሮ ርካሽ ነው፤ የኛ አይነት ሰዎች አሉ። ለውሀ አይከፈልም፤ የሀበሻ ማህበረሰቡም አለ። ስራም አገኘን። አሁን ያለንበት ቤት ከገባን ሶስት አመት ሆነን ማለት ነው። የእግዚአብሄር ስራ ነው፤ መንገዳችንን ያስተካከለልን እሱ ነው። በርግጥ በዚህ ሰአት ስራ የለንም፤ ሰራን ከተባለ አንድ ሺህ ሽልንግ ብንሰራ ነው። ከዛ ባለፈ ኦንላይን ላይ የምናውቀው ጓደኛ አለን፤ እሱ ያግዘናል። የዛሬን እንጂ የነገን አቅደን አድርገን አይደለም የምንኖረው። ከፊት እየቀደመ እያተስካከለልን ያለው እግዚአብሄር ነው።

በመንገዳችን ላይ እርስ በርስ ተደጋግፈን እዚህ ከመድረሳችን ባለፈ በሀሳብም በሁሉም ነገር ያገዙን የማህበረሰቡ አባላት አሉ። ቀድም የጠቀስነው የኦንላይን ጓደኛችን፤ በተለያየ ጊዜ ከጎናችን ነበር። ቤት ኪራይ እና አንዳንድ ወጪዎችን በቀናነት ይሸፍንልናል። በአካል እንኳን የማንተዋወቅ ልጅ ነው። በፌስቡክ ነው የምንተዋወቀው ግን በጣም ጥሩ እና መልካም አስተሳሰብ ያለው ሰው ነው። ሶስት አመት ሙሉ ቤት ኪራይ የከፈለልን እሱ ነው።

## ቤት፥ ነጻነት እና የኲዊር ማህበራዊ ህይወት

ግሬስ፡ ከነጻነት አንጻር ሲታይ ካደግኩበት ወግ አጥባቂ ቤት በማንነቴ ከምሸማቀቅበት ሀገር ወጥቼ በሰላም ሚስቴን አቅፌ ማደሬ ለእኔ ትልቅ ቁምነገርም ለውጥም ነው። ግን ሀበሻ ያለበት ቦታ እንደመኖራችን ሙሉ በሙሉ ነጻ ነን ማለትም አይደለም። ኬንያውያን እኮ በጣም ሰላም ናቸው። የሰው ጉዳይ ውስጥ አይገቡም። የማህበረሰባዊነት ስሜቱን በተወሰነ መልኩ ያገኘነው ከነሱ ነው። የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ጋር እናወራለን፤ እንገናኛለን። የሚገርምሽ ተያይተን እንተዋወቃለን። ማህበራዊ ህይወቱን አግኝተናል፤ ቤት የሚለውን ስሜት ደግሞ ሁልጊዜም ከኢትዮጲያ ጀምሮ ይዤው የመጣሁት ነው። ምክንያቱም ለእኔ ቤት ማለት አንዳችን ለአንዳችን መኖራችን ነው፤ ትንሿ ቤቴ ሚስቴ ነች። ይህም ለእኔ ትልቅ ቦታ አለው ምክንያቱም ኲዊር ማህበረሰቡ ላይ ያለው የፍቅር ግንኙነት ከባድ ነው።

እንደኔ እንደኔ ራስን መቀበል ብቻ ሳይሆን የወሰነ ሰው ማግኘት ይከብዳል ባይ ነኝ። ውሳኔ ላይ ያልደረሰ ሰው ፍቅር ውስጥ ገብቶ ሌላኛውን ሲያስለቅስ ብዙ ጊዜ አይቻለሁ። ጭራሽ ትዳር ውስጥ ሁሉ ይገባል። ዝግጁ ሳይሆን የራሱንም የሰውም ህይወት በማመንታት ያበላሻል። በሰምንት ሰባት ሰው ጋር ዴት ብታደርጊ ሰባቱም ላይወስኑ ይችላሉ። ማንነታቸውን ቢቀበሉም ዝግጁ ካልሆኑ ራሳቸውንም አንቺንም መምረጥ አይችሉም። በየመሀሉ ግራ ይጋባሉ።



“ ለብዙ ጊዜ የሚቆይልኝን ቁጥርጥር ሰርታኝ እንዲህ በራሷ ፉ እምር የምታደርገኝ የኔ አንድ እና ብቸኛ የኔ ዲዛይነር በሷ እጅ ሁሉም ያምራል 🥰 – ሄለን



“ "እጅህ ይዳብሰኝ ዞሮ በወገቤ" አይደል ያለችው? ሃሃ ልክ ብላለች! ሕይወቴ (ባለቤቴ ) ወገቤን ስታሸኝ ሰውነቴ ብቻ ሳይሆን ስሜቴ እራሱ ይስተካከላል ፣ ወደራሴ እመለሳለሁ።
የኔ ሁሉ ነገር የኔ ባለቤት ኑሪልኝ 🥰 – ግሬስ

> “ትንሿ ቤቴ ሚስቴ ነች። ይህም ለእኔ ትልቅ ቦታ አለው ምክንያቱም ኩዊር ማህበረሰቡ ላይ ያለው የፍቅር ግንኙነት ከባድ ነው። ”
>
> -ግሬስ



ዋነኛው ነገር ውሳኔ እና ራስን ተቀብሎ ለሚወዱት ሰው ታምኖ እና አምኖ መኖር ነው። እኔ ሄሉን ሳገኝ አለም ነው የሆነልኝ፤ ምክንያቱም ወስናለች። ወደኋላ የምታየው ነገር አልነበራትም። ማንነትን ተቀብሎ ለውሳኔ በቂ ጥንካሬ ሊኖረን ግድ ነው። እኔ ለምሳሌ እናቴ ላይ ጨክኜ ስወጣ እናቴን ጠልቼ አይደለም፤ ግን መወሰን እንዳለብኝ ካለበለዚያ የራሴን ጨምሮ የሁሉንም ሰው ህይወት እና እምነት ግራ እንደማጋባ ተረድቼ ነበር። ደግሞ መወሰንም ብቻ ሳይሆን በየእለቱ በውሳኔ መጠንከርም ያስፈልጋል። ብዙ ሰው ያንን ማለፍ ያቅተዋል።

## ብርታት እና የማንነት ኩራት

ሄለን፡ እግዚአብሄር አበርቺ ነው፤ እሱ ያበረታናል÷ አብዛኛውን ጊዜ ኩራት የተሳሳተ ትርጉም ቢኖረውም ፍቅራችን የእግዚአብሄር ስጦታ ነው እና ባለን ፍቅር እንኮራለን።

ግሬስ፡ ጠዋት ሲነጋ ሄሉን አጠገቤ ሳገኛት አበረታለሁ። እሷን ሳላይ ዋልኩ ማለት ቀኔ ይበላሻል። ከእግዚአብሄር ቀጥሎ የምታበረታኝ እሷ ነች። እሷ አለችኝ ማለት ሁሉ ነገር አለኝ ማለት ነው፤ የተሻለ ቀን እንዲመጣ የሚያጓጓኝ በመኖሬ ነው። ታጋይ መሆናችን፤ እዚህ በመድረሳችን እና ሳመንንበት፤ ነን ብለን ለተቀበልነው ነገር በመልፋታችን እና ኢየሱስ ስላለን እንኮራለን።


FIVE SHILLINGS
SHILINGI TANO
OF ETHIOPIA
PASSPORT
HOLY
BIBLE

ኩዊር ኢትዮጵያ
QUEER ETHIOPIA

ልዩ  እትም

ማህደር 2026 © መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

የማህበረሰባችንን የሕይወት ተሞክሮዎች እና ምስክርነቶቻቸዉን በታማኝነት ማጋራት።

